# የግብጹ ሁከትና ታላቁ የህዳሴ ግድብ!

**አሥራት ለማ**

ትግራይ ኦንላን May 14, 2014

ኢትዮጵያና ግብጽ ከአባይ ወንዝ ባሻገር በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሚተሳሰሩባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። በመሆኑም ግብጽ ውስጥ የሚፈጠር ቀውስ በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ኢትዮጵያን ሊጎዳ እንደሚችል መገመት የሚከብድ አይደለም፡፡ ከህዳሴው ግድብ ግንባታ ጋር ተያይዞም ቢሆን በዚያች አገር የተረጋጋ መንግሥት ቢኖር ይመረጣል።

በአንዳንድ የፖለቲካ መሪዎችና ምሁራን አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ እየቀረበ ቢሆንም ኢትዮጵያም ሆነች አብዛኛዎቹ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አካላት የግብጽን ሥጋት ለመቅረፍና ተጠቃሚነቷን እውን ለማድረግ በአገራቱ ዘንድ ጥልቅ ውይይትና ድርድር መካሄድ ብቸኛው አማራጭ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተው በመግለጽ ላይ ይገኛሉ፡፡

ኢትዮጵያም ሆነች ሌሎቹ አካላት ይህንን ምክራቸውን የሚለግሱት አሥር ያህል አገራት የሚጋሩትን የዚህን ወንዝ ውኃ አጠቃቀም በተመለከተ በተለይ በግብጽ በኩል የሚስተዋለውን ፈቃደኛ ያለመሆን አዝማሚያ በማጤኑና ጉዳዩ ከንትርክ አልፎ በሕዝቦች መካከል አላስፈላጊ ጥላቻ እንዳይፈጠር በመሥጋት ነው፡፡

አካላቱ ለውይይት አጽንኦት የሚሰጡት በንትርክና ውዝግብ ይህንንም ተከትሎ ሊፈጠር በሚችል ግጭት ጉዳት እንጂ ማንም ጥቅሙን ሊያረጋግጥ እንደማይችል ሙሉ እምነት ስላላቸውም ጭምር ነው የሚል እምነት አለ፡፡

እንዲያም ሆኖ ግን በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ከግብጽና በተወሰነ መጠን ከሱዳን በስተቀር በአብዛኛዎቹ የተፋሰሱ አባል አገራት የሚራመደው አቋም የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ የሚለው ቢሆንም በተለይ ግብጽ ይህንን አቋም ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የተቀበለችበት አጋጣሚ አይታይም፡፡

በግብጽ በኩል የሚስተጋባው ተቃውሞ በተለይ ከህዳሴው ግድብ ግንባታ ይፉ መሆን በኋላ የተባባሰ ቢሆንም ኢትዮጵያ ግን ጉዳዩን እያስተናገደችበት ያለው መንገድ በብዙዎች ዘንድ በጤናማነቱም ሆነ በውጤታማነቱ ሊጠቀስ የሚችል በጎ ተግባር ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን እያቀረቡት እንዳለው ዓይነት በጎ መፍትሄ በህዳሴው ግድብም ሆነ በአጠቃላይ በአባይ ወንዝ አጠቃቀም ዙሪያ በግብጽ በኩል ለሚነሱት ሥጋቶች ምላሽ ለመስጠት ለሚያስችል ውይይትና ድርድር በሯ ክፍት መሆኑን በተደጋጋሚ እያሳወቀች ነው፡፡ የአገሪቱ ባለሥልጣናትም በተለያዩ ወቅቶች በሚሰጧቸው መግለጫዎች ይህንኑ ሲያረጋግጡ ይደመጣል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ የግብጽ ፖለቲከኞችና ምሁራን ይህንን የኢትዮጵያ በጎ መንገድ የሚያፈርስ አቅጣጫ በመከተል በአገራቱ መካከል ጥላቻን የሚያነግሱ  ተግባራት ላይ ሲያተኩሩ ይታያል፡፡

እነዚህ ግብጻዊያን ጥላቻን ከማራገብ ባለፈ በኢትዮጵያ ላይ የተለያዩ ሴራዎችን በማሴር የአገሪቱን የልማትና ሠላም ሂደት ማደናቀፍን እንደ ሥልት መጠቀምን ሲሰብኩ እየተደመጡ ይገኛል፡፡

በእንዲህ ዓይነቶቹ የግብጽ አካላት ይህንን የመሰለና ከጥፋት ይልቅ ለማንም የማይጠቅም መንገድ ቢሰበክም ኢትዮጵያ ግን ከዚህ በተለየ ፍጹም ሰብዓዊነትንና ከምንኖርበት ዘመን ሥልጣኔ ጋር የሚጣጣም የዲፕሎማሲ አቅጣጫን ነው መከተል የመረጠችው፡፡

ይህ ደግሞ አገሪቱ ላለፉት ዓመታት የተከተለችውና በብዙ መልኩ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ውስጥ ለሚታዩት ሁለንተናዊ ለውጦችና አገሪቱንም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለተጎናፀፈችው እውቅና ምክንያት የሆነው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ነው፡፡
እዚህ ጋር የግብጽና የአባይ ወንዝ ጉዳይ ፖለቲካዊ ተረክ ገታ እናድርግና የአገራችንን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ያለፉት ዓመታት ስኬቶችን በጥቂቱ እናንሳ፡፡

ኢትዮጵያ ላለፉት 20 ዓመታት በምትከተለው የውጭ ፖሊሲ መሠረት የአባይ ወንዝ ጉዳይ የሁሉንም የተፋሰሱ አባል አገራት ተጠቃሚነት የሚረጋገጥበትን መንገድ ማመቻቸት፤ በዚህ ሂደትም ግብጽም ሆነች ሌሎች አገራት የማይጎዱበትን አቅጣጫ መዘየድ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ በአገሪቱ የተንሰራፋውን ድህነት ለመዋጋት የሚያስችል ጠንካራ የውጭ ግንኙነት መፍጠርን ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ በዚህ ፖሊሲ ሰነድ ላይ እንደተመለከተው ኢትዮጵያ ለዘመናት የምትታወቅበትን ድህነትና ኋላቀርነት በማሸነፍ አገሪቱንና ሕዝቦቿን በእድገት ለማራመድ ሠላም ወሣኝ መሆኑን ያገናዘበ ሥልትን ይከተላል፡፡

በመሆኑም የአገር ውስጥ ሠላምና መረጋጋትን ከማጠናከር ጎን ለጎን ከቅርብ የጎረቤት አገራት እና በተለያየ መልኩ ከኢትዮጵያ ጋር ቁርኝት ካላቸው የአካባቢው አገራት ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ሠላማዊ የትብበር ግንኙነትን መፍጠር የሚቻልበትን መንገድ ማመቻቸት የፖሊሲው አንኳር ተግባር ሆኖ እየተሰራበት ይገኛል፡፡

ከዚህ አኳያ የተለያዩ ማሣያዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ከሁለት አሥርተ ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ መንግሥት አልባ በሆነችው ሶማሊያ በአሁኑ ወቅት የተሻለ ሁኔታ እንዲፈጠር ግንባር ቀደም ሚናውን የተጫወተችው ኢትዮጵያ መሆኗን ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ጭምር መስክሯል፡፡

አሜሪካንን የመሳሰሉ ጠንካራ መንግሥታት ሞክረውት ያልተወጡትን ይህንን የሶማሊያ ችግር ከመፍታን አንጻር በኢትዮጵያ በኩል የተወሰደው እርምጃና የተከፈለው ሁለንተናዊ መስዋዕትነት የውስጥ ሠላምና መረጋጋት በውጫዊው ተመሳሳይ ሁኔታ ካልተደገፈ ፋይዳ እንደሌለው በመግለፅ አጽንኦት የሚሰጠውን የአገሪቱን የውጭ ፖሊሲ በሣልነትና ውጤታማነት ያሳያል፡፡

ሶማሊያዊያንን ተነግሮ ለማያልቅ ሥቃይና መከራ የዳረገውንና በመጀመሪያ በተለያዩ የጦር አበጋዞች፤ በኋላ ላይም አልሸባብን በመሳሰሉ ጽንፈኛ የኃይማኖት ቡድኖች ስትታመስ ለኖረችው አገር ሠላምና መረጋጋት ለመፍጠር ኢትዮጵያ የጀመረችውን የሚያበረታታ መንገድ በመከተል ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በተለይም የአፍሪካ ህብረት ሁነኛ ድጋፎችን እንዲሰጥ አድርጓል፡፡

በዚህም አማካይነት በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ከሁለት አሥርተ ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ አጥታው የነበረውን ቋሚ መንግሥት ማግኘት የቻለች ከመሆኑም ባሻገር ሕዝቦቿም መሠረታዊ

አገልግሎቶችን በአግባቡ አግኝተው የተረጋጋ ሕይወትን ለመምራት የሚያስችላቸው ሁኔታ እየተመቻቸላቸው እንደሚገኝ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አረጋግጧል፡፡

የአሁኑ የሱዳንና የደቡብ ሱዳን ፖለቲካ ሁኔታም የኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ ነፀብራቅ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ በሱዳን አያሌ ሺህዎችን ለሞት የዳረገውንና አገሪቱንም ለከፋ ድህነት አጋልጦ የቆየው የሱዳንና የቀድሞው ደቡብ ሱዳን ነጻ አውጪ ግንባር ጦርነት የመጨረሻ እልባት እንዲያገኝ ከማስቻል አኳያ የዚህች አገር ሚና የላቀ እንደነበርም በተለያዩ አጋጣሚዎች የተነገረ ሀቅ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከዚህም በላይ ከቅርብ ጎረቤት አገራት ባሻገር በምሥራቅ አፍሪካ ብሎም በመላው አፍሪካ አስተማማኝ ሠላምና ምጣኔ ሀብት እድገት እውን እንዲሆን የራሱን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡ ፖሊሲዋ የሠላም ፖሊሲ ነው፡፤ ለዚህም ነው ሠላምን ለማስከበር ከፍተኛ መስዋዕትነት እየከፈለች ያለችው።

ዘላቂ ልማት እውን የሚሆነው ሠላምና መረጋጋት ሲኖር መሆኑን በመገንዘብ አገሪቱ ለሠላም የተለየ ትኩረት ሰጥታ ተንቀሳቀሰች፡፡ በዚህም በአገር ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ሠላምንና መረጋጋትን በአስተማማኝ መልክ ማረጋገጥ ተቻለ፡፡

ይሁን እንጂ የአንዲት አገር ውስጣዊ ሠላም ብቻውን ዘላቂ ልማትን እውን ለማድረግ በቂ አለመሆኑን የተረዳው የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ለቀጣናው፣ ለአህጉሪቱና ለዓለም ሠላም መረጋገጥ የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ ማድረጉን ቀጠለበት፡፡

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት የውሣኔ ቁጥር 40 መሠረት የኢትዮጵያ የሠላም አስከባሪ ኃይል በ1986 ዓ.ም በሩዋንዳ ተሰማርቶ የፀጥታና የደህንነት ሽፋን በመስጠት ተልዕኮውን በአስተማማኝ መንገድ ተወጣ፡፡

በሁለት ዙር በሩዋንዳ የተካሄደውን ዘመቻ በሚመለከት ሮሚዮ ዴለር የተባሉ ጄኔራል ምስክርነታቸውን ሲሰጡ "በሩዋንዳ የተሰማራው የኢትዮጵያ የሠላም አስከባሪ ኃይል በሁቱዎችም ሆነ በቱትሲዎች ዘንድ ተቀባይነትንና ተወዳጅነት ማግኘት ችሏል፤ ይህንን ተዓማኒነትና ተወዳጅነትን ያገኘው ግን በሚጠቀመው ኃይል አልነበረም፡፡

ሠራዊቱ በጥሩ ሥነ ምግባር ከመታነጹም በላይ ለአካባቢው ሕዝብ በሚያደርገው የተለያየ እገዛና በሚያሳየው ፍቅር ነው፡፡ ሠራዊቱ ለማንኛውም ነገር አይቸኩልም፤ ሁሉንም በትዕግስት ይከታተላል፡፡ ጸጥታውን በአስተማማኝ መንገድ በመጠበቅ በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ሕዝቡን ያግዛል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ተግባር በሌሎች ዘንድ ያልተለመደ ነው፡፡" ብለዋል፡፡

እንደ ጄኔራሉ ምስክርነት የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ሠራዊት ሠላምንና ጸጥታን ከማስጠበቅ ጎን ለጎን ለኅብረተሰቡ የጎላ ፋይዳ ያላቸው ልማቶችን በሚንቀሳቀስበት አካባቢ ይሰራል ብለዋል፡፡

በኮንጎ የአካባቢው ሕዝብ ወደ ዛየር የሚተላለፍበት መንገድ እጅግ ጠባብና አስቸጋሪ እንደነበረ ገልጸው፤ የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ሠራዊት ለመተላለፊያ አመቺ የሆነ ደልድይ መሥራቱንም አስታውቀዋል፡፡ በተጨማሪም ገበሬው ማሣ ድረስ በመሄድ እህሉን በማጨድና በመውቃት እንደሚያግዝ ተመልክቻለሁ ብለዋል፡፡

ሠራዊቱ በሄደበት አገር ሁሉ ለሕዝብ በሚሰጠው ከፍተኛ አክብሮትና ፀረ ሠላም ኃይሎችን በመደምሰስ ረገድ በሚያሳየው ጀግንነት ተወዳጅ ሆኗል ይላሉ ጄኔራሉ፡፡ በመሆኑም የሩዋንዳው ተልዕኮ ሥኬት አፍሪካውያን ችግራቸውን በራሳቸው መፍታት እንደሚችሉና ከምዕራቡ የሚያስፈልጋቸው የገንዘብና የሎጀስቲክስ ድጋፍ ብቻ እንደሆነ ያስመሰከረ ነበር፡፡

በቡሩንዲ መንግሥትና በአማጺያን መካከል የተደረሰው የአሩሻያ ተኩስ አቁም ስምምነት ተግባራዊ ባለመሆኑ የሠላም አስከባሪ ኃይል በቦታው እንዲሰፍር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በመወሰኑ የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ሠራዊት ወደ ቡሩንዲ ተሰማራ፡፡

ቡሩንዲ በእርስ በርስ ጦርነት በመዳከሟ በአገሪቱ የሚደረጉ የሠላም ጥረቶችን ለመደገፍ ኢትዮጵያ አንድ ሺህ ሠላም አስከባሪ ሠራዊት ወደ ሥፍራው ልካለች፡፡ በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የዘመቻውን መጀመር አስመልክተው የሠላም አስከባሪ ኃይል ተልዕኮውን እንደሚወጣ አምነታቸው እንደሆነና የአፍሪካ ህብረት በእምነት የሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ እንደሚፈጽም በማረጋገጥ ይህ ለኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ኩራት እንደሚሆን እተማመናለሁ ብለው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ሠራዊትም የተሰጠውን ኃላፊነት በተገቢው መንገድ መወጣት ችሏል፡፡

ኢትዮጵያ የተሳተፈችበት ሌላው ተልዕኮ በላይቤሪያ ነበር፡፡ ተልዕኮው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት በቁጥር 1509 ባስተላለፈው ውሣኔ መሠረት የተኩስ አቁም ስምምነቱን መፈፀሙን መቆጣጠር፣ ትጥቅ ማስፈታትና ሠላምን ማረጋገጥ የሚል ኃላፊነት ነበር የተሰጠው፡፡ ሠላም አስከባሪው ቀጣይነት ያለው ሠላም ለማምጣት ተግቶ በመሥራቱ ከላይቤሪያውያን የተሰጠው እውቅናና ከብር የላቀ ነበር፡፡

የሠላም አስከባሪው አዛዥ የነበሩት ብርጋዴር ጄኔራል ሥዩም "ከላይቤሪያውያን ወንድሞችና እህቶቻችን የተለያዩ ድጋፍና ትብብር በማግኘታችን ሁልጊዜም አገራችን ውስጥ እንዳለን ይሰማናል፤ ስለዚህም ተልዕኳችንና ኃላፊነታችንን ለመወጣት በጣም ረድቶናል።" ብለው ነበር፡፡

በላይቤሪያ ተሰማርቶ የነበረው የኢትዮጵያ የሠላም አስከባሪ ኃይል ከ13 ሺህ በላይ አማጽያንን ትጥቅ በማስፈታትና ከ21 ሺህ 629 በላይ ስደተኞች ወደቀያቸው እንዲመለሱ ማድረግ ችሏል። ከዚህም በተጨማሪ በአገሪቱ ሠላማዊ ምርጫ እንዲካሄድ የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

ኢትዮጵያ የውስጥ ሠላሟን በአስተማማኝ መንገድ በማረጋገጥ በአፍሪካ አህጉር ያለውን ሁከትና ብጥብጥ ለማርገብ በሚደረገው ጥረት ያላት የጎላ ተሳትፎ በሶማሊያና በሱዳንም ቀጥላበታለች፡፡

የሶማሊያ ሕዝብ ላለፉት 30 ዓመታት በእርስ በርስ የጎሳ ጦርነቶች ተዘፍቆ በአገሪቱ ሠላምና መረጋጋት ጠፍቶና ሁከትና ሽብር ተንሰራፍቶ የእለት ተለት ኑሮውን ለመምራት የማይችልበት ሁኔታ ተፍጥሮ ቆይቷል፡፡

ይህንኑ ክፍተት የተገነነዘበው የአልቃይዳ የምሥራቅ አፍሪካ ክንፍ የሆነው አልሸባብም አገሪቱን ተቆጣጠረ፡፡ ከዚያም በኢትዮጵያ ላይ ጅሃድ አወጀ፡፡ የኢትዮጵያ ልማትን ለማደናቀፍና አገሪቱ እያስመዘገበችው ያለውን እድገት ለማደናቀፍ ከኤርትራ መንግሥት ጋር ግንኙነቱን በማጠናከር እንቅስቃሴ ጀመረ፡፡

በኢትዮጵያ የሰፈነው ሠላም አገሪቱ በልማቱ ረገድ ጥሩ ውጤት እንዳስገኘላት የተገነዘበው የሻዕቢያ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ባካሄደው እብሪተኛ ጦርነት ቅስሙ ተሰብሮ የተመለሰ ቢሆንም በእጅ አዙር የኢትዮጵያን ሠላም ለማደፍረስ የተለያዩ አጀንዳዎችን ነድፎ መንቀሳቀሱን አላቆመም፡፡

ከዚህም ሌላ አገሪቱ ሠላም በራቀቻው የተለያዩ የአፍሪካ አገራት ውስጥ በተካሄዱት የሠላም ማስከበር ተግባራት በቀዳሚነት በመሳተፍ ለየአገራቱ ሕዝቦች ያላትን ወገንተኝነት ያሳየችውም በዚሁ ለሠላምና ልማት ትኩረት በሚሰጠው የውጭ ፖሊሲዋ አማካይነት ነው የሚል እምነት አለ፡፡

ይህ ውጤታማ የሠላም ማስከበር ተግባሯም በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ ተመራጭ አገር እንድትሆን አስችሏታል፡፡ አሁንም ቢሆን ይህች አገር ከራሷ ምድር ባለፈ ለተቀረው የአፍሪካ አገር ሁሉ ሠላምና ልማትን ትመኛለች፡፡ ከዚህ አኳያ በአሁኑ ወቅት ግብጻዊያን ታላቅ ፈተና ውስጥ የከተተው የፖለቲካ አለመረጋጋት ከምንም በላይ ከሚያሳስባቸው አገራት መካከል ኢትዮጵያ ቀዳሚዋ ነች ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

ምክንያቱም ኢትዮጵያ ከሶማሊያ፣ ሱዳንና መሰል የቅርብ ጎረቤት አገራት ባልተናነሰ ለግብጽ ትኩረት የምትሰጠው ሁለቱን አገራት በተፈጥሮ ያስተሳሰራቸው የአባይ ወንዝ ውኃ መኖሩ ብቻ ሳይሆን የውጭ ፖሊሲዋ ለግብጽ ሕዝብ ሠላምና መረጋጋት እንድትሰራ የሚያስገድዳት በመሆኑም ጭምር ነው፡፡

ከአንድ ዓመት በፊት በሕዝባዊ ምርጫ ሥልጣን ይዘው የነበሩት የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ሙሐመድ ሙርሲና ፓርቲያቸው ሙሥሊም ብራዘር ሁድ በግብጽ በተካሄደው ሕዝባዊ የተቃውሞ ሰልፍ ተከትሎ በወታደራዊው ኃይል ግፊት ከኃላፊነታቸው ከመነሳታቸው ጋር በተያያዘ አገሪቱ በተከታታይ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች እየታመሰች ነው፤ በዚህም ምክንያት በየጊዜው ሕይወቱ የሚያልፈው የአገሪቱ ዜጋ ቁጥር እያደገ ይገኛል፡፡

በአገሪቱ እየተስተዋለ ባለው የፖለቲካ አለመረጋጋት ችግር ውስጥ ወድቆ የነበረው የአገሪቱ ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታም በአሁኑ ወቅት እየተባባሰ በመጣው ግጭት ሣቢያ የከፋ ሁኔታ ውስጥ ገብቶ ችግሩ ወደከፋ አደጋ እንዳይሸጋገር የብዙዎች ሥጋት ሆኗል፡፡

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብም ያለው አመለካከት ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ አልአህራም ባቀረበው ዘገባ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን የግብጽን ወቅታዊ ሁኔታ በየቀኑ በመከታተልና በመዘገብ ላይ ይገኛሉ ሲል በዝርዝር አትቷል፡፡

የኢትዮጵያ ጋዜጦች የግብጽ አለመረጋጋት ለጎረቤት አገራት ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ አሉታዊ ችግር ሊፈጥር የሚችል በመሆኑ ትኩረት ሊቸረው ይገባል ሲሉ በመዘገብ ላይ መሆናቸውንም አልአህራም ጨምሮ ጠቁሟል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት መግለጫና የአገሪቱ መገናኛ ብዙኃን ዘገባዎች የሚያሳዩት የግብጻዊያን ጉዳይ የኢትዮጵያዊያንም ጭምር መሆኑን ነው፡፡ እናም ይህ የኢትዮጵያ መንግሥት አቋምና በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት የሚስተጋባው የሕዝብ አስተያየት አንዳንዶች ግብጽ ውስጥ አሁን የተፈጠረው የፖለቲካ አለመረጋጋት ለኢትዮጵያ መልካም አጋጣሚ ነው በማለት የሚሰጡት አስተያየት የተሳሳተና ከሰብዓዊነት አንጻርም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ኢትዮጵያ  ለግብጽና ሕዝቦቿ የምታስብና የምትቆረቆር አገር መሆኗን በተጨባጭ ያሳየችበት አንድ ወሣኝ ሁነትን እንጥቀስ፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ይፋ በሆነበትና የአባይ ተፋሰስ አባል አገራት ለዓመታት ሲመክሩበት ቆይተው ስድስቱ የአባይ ወንዝን ፍትሃዊ አጠቃቀም ያረጋግጣል የተባለውን ሰነድ በይፋ የተቀበሉበት ወቅትና የግብፁ የረዥም ዘመን መሪ ሁስኒ ሙባረክ በሕዝባዊ አብዮት ከሥልጣናቸው የተባረሩበት ወቅት ተገጣጥሞ ነበር፡፡

ከዚሁ ጋርም ሰነዱን በተለይ ግብጽ ከፉኛ በመቃወሟ የስምምነቱ አካል እንደማትሆን ገልፃ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ሰነዱን የተቀበሉት የተፋሰሱ አባል አገራት ግብጽ የዚህ ስምምነት አካል እንድትሆንም ብርቱ ፍላጎት ነበራቸው፡፡

ምንም እንኳ የተፋሰሱ አባል አገራት ሰነዱን ለየአገሮቻቸው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች በማቅረብ ማስፀደቅ ይጠበቅባቸው የነበረ ቢሆንም ወቅቱ በግብጽ የተረጋጋ መንግሥታዊ ሥርዓት ገና ያልተፈጠረና በአገሪቱም አስተማማኝ መረጋጋት የሌለ መሆኑን በመገንዘብ ስምምነቱን የመንግሥት ህግ የሚደረግበትን ጊዜ በማዘግየት በግብጽ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት እስኪመሠረት ለመጠበቅ ለግብጽ መንግሥት ቃል ገብተው ነበር፡፡

በዚህ ረገድ የመጀመሪያውን እርምጃ በመውሰድ ለግብጽ መንግሥት ቃሏን ያረጋገጠችው ኢትዮጵያ ነበረች፡፡ የግብጽ መንግሥት አሁንም ድረስ ሰነዱን ለመቀበል ዝግጁነት እያሳየ ባይሆንም  ኢትዮጵያ ሰነዱ ለግብጽም ጭምር ሊኖረው የሚችለውን ጥቅም ከማስረዳት አንስቶ በአባይ ወንዝ ላይ የሚገነባው የህዳሴው ግድብ ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን በዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ጭምር እንዲረጋገጥ አድርጋለች፡፡

ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ዓለም አቀፍ ሙያተኞችም ሆኑ የፖለቲካ ሰዎች ግብጽ የአባይ ወንዝ ተጠቃሚነቷን ማረጋገጥ የምትችለው ከአባል አገራቱ ጋር ተቀራርባ በመሥራት እንጂ ራሷን በማግለል አይደለም ሲሉ የኢትዮጵያን አቋም የሚደግፍ ምክራቸውን ከመለገስ አልተቆጠቡም፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን መቃኘት የሚችል የኢትዮጵያ መንግሥት የሚከተለው የፖለቲካ ኢኮኖሚ መርህ እና ፍልስፍና በአገሪቱ ምድር ላይ በሚፈጠሩና በሚከወኑ ኩነቶች ላይ ብቻ የሚመሠረት አይደለም፡፡ ከዚህ ባሻገር የሚሄድ ተራማጅ እና ከራስ ባለፈ ለሌሎችም ጥቅም የቆመ ፖሊሲ መሆኑንም ይገነዘባል፡፡

በግብጽ ያለው ሁከትና ብጥብጥ ለቀጠናው ሠላም መደፍረስም የበኩሉ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በተለይ ከኢትዮጵያ ጋር ቋሚ የሆነ ስምምነት ለማድረግ አዳጋች ይሆናል። በየሦስት ወሩ ጠቅላይ ሚኒስትር በሚቀያየርባት አገር የሚደረግ ስምምነት ምን ያህል ውጤታማ ይሆናል? ይህ ከንቱ ነገር ነው።

ስምምነትማ ካሁን ቀደም የግብጽ ሕዝብ ዲፕሎማሲ ወደ አዲስ አበባ በመጡበት ወቅትና ከዚያ በኋላ በተቋቋመው መንግሥት ጋር ውይይቶች ተካሂደው ስምምነቶች ተደርገው እንደነበሩ ይታወቃል።

ይሁን እንጂ መንግሥት በተለዋወጠ ቁጥር የአቋም ለውጥ ስለሚመጣ አስተማማኝ ስምምነት ይደረጋል ተብሎ አይታሰብም። ለዚህም ነው በግብጽ ያለው ሁከትና ብጥብጥ ለሌሎች አገራትም ይተርፋል ለማለት የሚያስደፍረው።